# በምትክነት ስለሚገቡ እቃዎች

# የወጣ ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያ

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

ነሐሴ 2001 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

# በምትክነት ስለሚገቡ እቃዎች የወጣ ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 31/2001

ለአገር ውስጥ ፍጆታ ተብሎ የገባ ዕቃ ተመልሶ ከአገር የሚወጣበትንና በምትኩ ተመሣሣይ ዕቃ የሚገባበትን ስርዓት በመመሪያ መደንገግ በማስፈለጉ፣

በምትክነት በሚገባ ዕቃ ላይ ሊወሰድ የሚገባውን የጥንቃቄ እርምጃ፣ ስለፈቃድ አሰጣጡና ስለቁጥጥር አፈፃፀም ወጥ በሆነ አግባብ አሠራሩን መግለጽ በማስፈለጉ፣

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 58(2) በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያ አውጥቷል።

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "በምትክነት ስለሚገቡ ዕቃዎች የወጣ ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 31/2001" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## 2. ትርጓሜ

ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ሲባል፦

1) "ዕቃ" ማለት ወደ አገር ከገባ በኋላ፣ በስህተት፣ በብልሽት፣ ለታለመለት ዓላማ ሊውል የማይችል በመሆኑ ወይም ያልተሟላ በመሆኑ ተመልሶ እንዲወጣ ጥያቄ የቀረበበትና በባለሥልጣኑ ፈቃድ የተሰጠው ዕቃ ሲሆን በምትኩ የሚገባ ተመሣሣይ ዕቃን ይጨምራል።
2) "ዕቃን መልቀቅ" ማለት በጉምሩክ ቁጥጥር ሥር ያለ ዕቃ ለተገለፀለት ዓላማ እንዲውል በባለስልጣኑ የሚለቀቅበት ስርዓት ነው።
3) "በስህተት የመጣ ዕቃ" ማለት ወደ አገር የገባው ዕቃ በዲክላራሲዮን ላይ ከተመዘገበው ዕቃ ጋር በመጠን፣ በጥራትና መሰል መመዘኛዎች የተለየ ሆኖ የተገኘና አስመጪው የማይፈልገውና መልሶ የሚልከው ነው።

4) “ያልተሟላ ዕቃ” ማለት ወደ አገር የገባው ዕቃ ለባለሥልጣኑ መግለጫ ከቀረበበት ዕቃ በቁጥር፣ በመጠን፣ በክብደት፣ እና በመሳሰሉት ምክንያቶች የጐደለ ወይም ያነሰ ዕቃ ነው፡፡

5) “ተመሣሣይ ዕቃ” ማለት ወደ አገር እንዲገባ ለባለሥልጣኑ መግለጫ ከቀረበበት ዕቃ ጋር በስያሜው፣ በአካላዊ ባህሪው፣ በጥራቱ፣ በተፈላጊነቱ፣ በንግድ ምልክቱ እና በስራቱ አንድ ዓይነት የሆነና በምትክነት የመጣ ወይም የሚመጣ ዕቃ ነው፡፡

6) “አስመጪ” ማለት ዕቃን ወደ አገር ውስጥ የሚያስገባ ማንኛውም ሰው ነው፡፡

7) “ላኪ” ማለት አገር ውስጥ ላለ አስመጪ ከውጭ አገር ዕቃ የሚልክ ወይም የሚያቀርብ ሰው ነው፡፡

8) “ዋራንቲ ሰርተፊኬት” ማለት ማንኛውም ላኪ ለዕቃ ተቀባይ ወይም ለአስመጪው ስለላከው ዕቃ የሚሰጠው ዋስትና የተገለፀበት ሰነድ ነው፡፡

9) “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ነው፡፡

10)“ባለሥልጣን” ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ነው፡፡

11)“አዋጅ” ማለት የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 ነው፡፡

## 3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ ለአገር ውስጥ ፍጆታ ሲባል ወደ አገር የገባ ዕቃ በጉምሩክ ቁጥጥር ስር እያለ ባለስልጣኑ በሚሰጠው ፈቃድ ከአገር ወጥቶ በምትኩ በሚገባ ተመሳሳይ ዕቃ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 4. <u>ማመልከቻ ስለማቅረብ</u>

ማንኛውም አስመጪ ለአገር ውስጥ ፍጆታ ሲባል ያስገባው ዕቃ፡-

ሀ/ ስህተት ያለበት፣

ለ/ የተበላሸ፣

ሐ/ ለታለመለት ዓላማ መዋል የማይችል፣

መ/ ያልተሟላ መሆኑን፣ ወይም

ሠ/ በሌሎች ተመሳሳይ ምክንያቶች፣

መኖራቸውን ከተረዳ ዕቃው በባለስልጣኑ ከመለቀቁ በፊት ወደ መጣበት አገር እንዲመለስና በምትኩ ተመሣሣይ ዕቃ ለማስገባት እንዲፈቀድለት ዕቃው ለገባበት የባለሥልጣኑ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በጽሑፍ ማመልከት ይኖርበታል፡፡

## 5. ከማመልከቻ ጋር ተያይዘው ስለሚቀርቡ ሰነዶች

አስመጪው በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 መሠረት ጥያቄ ሲያቀርብ የሚከተሉትን ሰነዶች ከማመልከቻው ጋር ማያያዝ ይኖርበታል፡፡

1) ወደ አገር የገባው ዕቃ የተመዘገበበትን የጉምሩክ ዲክላራሲዮን ኮፒ፣
2) ቀደም ሲል ከዲክለራሲዮኑ ጋር በአባሪነት ለባለሥልጣኑ የቀረቡ ሰነዶች በሙሉ ኮፒ፣
3) ላኪው ስለ ዕቃው የሰጠው ዋራንቲ ሰርተፊኬት ከዋናው ጋር የተመሣከረ ኮፒ፣
4) አስመጪው በዋራንቲ ሰርተፊኬቱ ላይ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ከአገር እንዲወጣ እና በምትክ ተመሣሣይ ዕቃ እንዲላክለት ለላኪው ጥያቄ ያቀረበበትን ኮፒ፣ እና
5) ላኪው ዕቃው እንዲመለስለትና ተመሣሣይ ዕቃ እንደሚልክ የገለፀበትን ደብዳቤ ከዋናው ጋር የተመሳከረ ኮፒ፡፡

## 6. ውሣኔ ስለመስጠት

የባለሥልጣኑ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሥራ አስኪያጅ በዚህ መመሪያ መሠረት የሚቀርብለትን ጥያቄ በመመርመር በአምስት የስራ ቀናት ውስጥ ውሣኔ ይሰጣል፡፡

## 7. ስለ ቀረጥና ታክስ ክፍያ

1) በዚህ መመሪያ መሠረት በምትክነት ለሚገባ ዕቃ ቀረጥና ታክስ አይከፈልበትም፡፡
2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም በምትክነት የመጣው ዕቃ ቀደም ሲል በስህተት ገብቶ ከነበረው ዕቃ ጋር በዋጋ፣ በመጠን እና ከመሰል መመዘኛዎች አንፃር ከአምስት በመቶ (5%) ያልበለጠ ልዩነት ያለው ከሆነና

አስቀድሞ ለዕቃው ከተከፈለው ቀረጥና ታክስ በተጨማሪ የሚያስከፍል ሆኖ ከተገኘ ተጨማሪ ቀረጥና ታክስ ይከፍላል፡፡

3) የተገኘው ልዩነት ከአምስት በመቶ (5%) የበለጠ እንደሆነ በጉምሩክ ሥራ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን በአስተዳደራዊ ውሣኔ ለመጨረስ በወጣው መመሪያ መሠረት ይስተናገዳል፡፡

## 8. <u>አስቀድሞ የገባን ዕቃ ስለመላክ</u>

1. በዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች መሠረት ወደ አገር እንዲገባ የተጠየቀው ምትክ ዕቃ በስህተት የመጣው ዕቃ ተመልሶ ከአገር ለመውጣቱ ከኢትዮጵያ መውጫ ከሆነው የመጨረሻ ጣቢያ ከሚገኝ የባለስልጣኑ ጽ/ቤት ማስረጃ ካልቀረበ በቀር ወደ አገር ሊገባ አይችልም፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ከአገር እንዲወጣ የሚላከው እቃ በአጃቢ መሆን ይኖርበታል፡፡

## 9. <u>ተመልሶ ለሚላከው ዕቃ ስለሚከፈል ክፍያ</u>

ወደ አገር የገባው ዕቃ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 መሠረት ተመልሶ ከአገር እንዲወጣ ሲፈቀድ በአዋጁ አንቀጽ 57 (1) መሠረት የቀረጥና ታክሱን 5 በመቶ ይከፈልበታል፡፡

## 10. <u>ክልከላ</u>

1) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 (2) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በምትክነት ወደ አገር የሚገባ ዕቃ ወደ መጣበት አገር እነዲላክ ከተደረገው ዕቃ ጋር ተመሳሳይ ካልሆነ በቀር ወደ አገር ማስገባትም ሆነ እንዲገባ መፍቀድ የተከለከለ ነው፡፡
2) ባለሥልጣኑ በምትክነት የገባው ዕቃ ተመሣሣይ ያልሆነ እንደሆነ በአዋጁ አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች መሠረት ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል፡፡

## 11. <u>የተሻሩ መመሪያዎችና ሰርኩላሮች</u>

ይህንን መመሪያ የሚቃረኑ መመሪያዎች፣ ሰርኩላሮች እና የአሠራር ስርዓቶች በሙሉ በዚህ መመሪያ ተሽረዋል፡፡

## 12. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ተፈርሞ ከወጣበት ዕለት ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ__________ ቀን 2001 ዓ.ም.

መላኩ ፈንታ
የኢትዮጵያ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
ዋና ዳይሬክተር